# በፍቅር የተያያዙ ትውልዶች

ካህን ራስል ኤም ኔልሰን
የአስራ ሐለቱ ሐዋሪያት ቡድን አባል

በጌና የሚንቀበለው ደብዳቤ ስለ ውድ ጓደናችን እና ዘመዳችንንን ትውስታ ያመጣል። አንዳንዶቹ መልዕክቶችም ቤበተሰብ ፍቶ የዳበሩ ናቸው። ትኩረት ያመጣብኝ ይህ ነው።

ይህ አንዱ የልጅ ልጃችን ሴት ልጅ ነው።ውድ ሩብ እላታለሁ። ይህ ፎቶ እናቷ በዝሁ ዕድሜ ባለችበት   መሆኑን ያስታውስውኛል። ውድ ሩብ የልጅ ልጃችን ናት።

ይህን ፍቶ የወሰድኩት ወደ ሀያ ዘጠኝ አመት ይጠጋል። አይኗ እስካሁንም ሰማያዊ ነው።

ልጃችን የሩብ እናት ህፃን በነበረች ከግማሽ ክፍለ ዘመን ትውስታን እናገኛለን። ይህ አንዱ የህፃንነቷ ፎቶ ነው። አሁን እሷ የሴት አያት ስትሆን እኔ ቅድመ አያት ነኝ። የህፃንነቴን ፎቶ አላሳያችሁም። ልረዳም አይችልም። ይህ ፎቶ የአራት ትውልድን ፍቅር ያሳያል።

ስለያንዳንዱ ቤተሰባችን ፍቅር ሳስብ የሰማይ አባት ለልጆቹ   ያለውን ፍቅር ይሰማኛል። ቤተሰቦች በአለማት ደረጃ እየተጠቁ የኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስትያን ቤተሰቦች በፈጣሪው ዘላለማዊ ዕቅድ ዋነኛ እንደሆኑ እውነትን በመከላከል ያውጃሉ። የቤተሰብ ለአለማት አዋጅ እና   ሰፋ ያለ የቤተሰብ ታሪክ ጥረት ይህ ቤተክርስትያን ተስፋን ማምጣት እና ቅዱስ የቤተሰብ እንትቱሽን የሚረዳ ሁለቱ መረጃዎች ናቸው።

እግዚአብሄር ለልጆቹ ያለው ፍቅት ወሰን እንደለለው እናስተምራለን። ካለዘር፤ ዜግነት ወይም ፆታ ሁላቸውንም ይወዳል። ይህን ከመጀመሪያው ጀምሮ አድርገዋል ለወደፍትም ያደርጋል። ሁሉ ቤተሰቦች ዘላለማዊ ህይወትን እንድያገኙ ሁሉንም ይጋብዛል። ሥራው እና ክብሩ ህያውነትን እና ዘላለማዊ ህይወትን ለልጆቹ ለማምጣት ነው።   በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

የተወደደው ልጁ ሀጢአት ክፍያ ሁለቱን የአባት አላማዎች እንድሚላ አድርገዋል። ከሀጢአት ክፍያ ውጭ ህያውነት አይኖርም። ከሀጢአት ክፍያ ውጭ ወደ ሰማይ አባት

መመለስ እና ከሞት በኋላ የቤተሰብ መቀጠል አይኖርም።

በሀጢአት ክፍያ ምክንያት እያንዳንዱ የግዚአብሄር ልጆች ዘላለማዊ ህጉ ታዛዥ ከሆኑ ከፍተኛውን በረከቶችን ይገነዘባሉ። በምድር ታሪክ ብዙዎች ልጆቹ ወን ጌልን ለማግኘት ዕድል ብያጋጥማቸውም ግን ብዙዎቹም አላገኙም። ምድር ከመፈጠሩ በፍት ካለወንጌል ዕውቀት ለሞቱት የሰማይ አባታችን የጥምቀት ሥርዓቶችን አቋቁመዋል። እነኝህንም ልጆች ይወዳል።

ዘላለማዊ ቤተሰብ አካል እንድሆኑም መንገድ አዘጋጅተዋል። ወደዚህ ምድር የመጣው ማንኛውም የሰው ዘር የቅድመ አያቶች ትውልድ ቤተሰብ ውጤት ናቸው። ከቅድመ አያቶቻችን ጋር የመገናኘት ተፈጥሮአዊነት አለን። ይህም ፍላጎት ካለ ዕድሜ ገደብ በልባችን ይሆናል።

ወጣት ሴት አያቷን በመርዳት ስለቤተስብ ሁነታ ወደ ኮምፒዩተር ውስጥ ስታስገባ መንፈሳዊ ግንኙነታቸውን አስቡ። ወይም ወጣት ወንድ የቅድመ አያቱን ስም በህዝብ ቆጠራ መዝገብ ላይ ማየቱን አስቡ። ልባችን ወደ ቅድመ አያቶቻችን ስዞር በውስጣችን ለውጥ ይመጣል። ከራሳችን የበለጠ ነገር ይሰማናል። ቤበተመቅደስ ቅዱስ ሥርዓቶች ከቅድመ አያቶቻችን ጋር ስንያያዝ በተፈትሮ ለቤተሰብ የመኃኃት ግንኙነታችን ይሚላል።

በዚህ ጠቃሚ ሥራ ምክንያት ቤተክርስትያን ሰዎች ወደ ምቀርባቸው ቦታ ቤተመቅደስን ገንብተዋል። የቤተሰብ ታርክ ጥናትም ከመቼውም የበለጠ ምቾት አግኝተዋል። ለቤተመቅደስ ሥርዓቶች ስምን የመፈለግ ዛዴዎችም እየተሻሻሉ መጥተዋል። በጥቅምት ሁለትሺ አምስት ጉባኤ ላይ ፕሬዝዳንት ሂንክል ለቤተሰብ ታሪክና ቤተመቅደስ ሥራ የነበረውን ደረጃ አስታውቆ ነበር። እሳቸውም አሉ- ስለ ቤተመቅደስ እንቅስቃሴዎች ረባሽ የሆነው ገፅታ ብዛት ያለውን ቤተመቅደስ እያገኘ ስንመጣ በውክል ሥራ የተባዛ ጥረት እንድሚኖር ነው። ...መፍትሄውም በተወሳሰበው ኮምፕዩተር ቴክኖሎጅ ላይ ይሆናል።

ከዚያ ጀምሮማባዛቱም ልቀንስ አልቻለም፤ ግን ቅደም ተከተሎች የቤተክርስትያን አባሎች ለቤተሰብ ታሪክ ሥራ እንድሳተፉ ቀለልተኛ ሆነዋል። ይህ ቅዱስ ሥራ ከአሁን በኋላ በሙያተኛ ብቻ ልሰራ አይችልም። ሁነታችሁ የፈለገ ብሆንም የቤተሰብ ታሪክን አሁን ከኑሮአችሁ አካል ማድረግ ትችላላችሁ። ልጆች የቤተሰብ ዛፍን መሳል ይችላሉ። ወጣቶች በጥምቀት ወኪልነት መሳተፍ ይችላሉ። አዛውንት ትውልዶችንም በኮፒዩተር መርዳት ይችላሉ። ወላጆች የራሳቸውን ታሪክ ከመጪው ትውልድ ጋር

ማዛመድ ይችላሉ። ጎልማሳ አባላቶች የቤተመቅደስ መግቢያ ፍቃድ በብቃት በመያዝ ለራሳቸው ቤተሰብ የቤተመቅደስ ሥርዓቶችን መፈፀም ይችላሉ።

ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ አሉ- በዚህ ምድር እግዚአብሄር የሰጠን ታልቅ ሀላፍነት የሞቱትን መፈለግ ነው። አድስ ስልጣኔ ከመቼውም ሀላፍነቱን ለመወጣት ቀላል አድርገዋል። ቤተመቅደስና የቤተሰብ ታሪክ አሁን የቤተሰብ አድስ ፍለጋ በሚለው ዛዴ የተመቼ ሆነዋል። ይህ እንተርኔት አባሎች ትውልድቸውን በመለየት ተገቢውን የቤተመቅደስ ሥርዓቶችን እንድሰራ ይረዳቸዋል። እንተርነት ባለበት ከቤትም ልደረግ ይቻላል። ደረጃውም ለመከተል ቀላል ነው።

መጀመሪያ የቤተመቅደስ ሥራ ለመሥራት ፍላጎት ያደረባችሁን ግለሰቦች ለዩ።

ከዚያ የቤተሰብ ሥርዓት ጥያቄዎችን አትሙ። ይህ የመረጃ ማስታወቂያ ቤበተመቅደስ ይፈለጋል።....

ከቤተሰብ ሥርዓት መጠይቅ የሥርዓት መታወቂያ ወረቀት ቤበተመቅደስ ይታተማል። ሥርዓቱ ከተፈፀመ በኋላ በዛኑ ቀን ወደ አድሱ የቤተሰብ ፍለጋ መዝገብ ላይ ይገባል።

to you.
እናንቴ ኮፒዩተር የሌላችሁትስ? አታስቡ! አንድ እርምጃ ውሰዱ። እቤት ጀምሩ። በፕሬዝዳንት ቦይድ ኬ ፓኬር አስተያየት እንደተሰጠው በባዶ የወረቀት ሳጥን ውስጥ የቤተሰብ ጠቃሚ በረጃዎችን አስቀምጡ። ከሌሎች ቤተሰባችሁ የተሰበሰበውን መረጃም ጨምሩበት። ከዚያ በኋላ እርዳታን ጠይቁ። አድሱ የቤተሰብ ፍለጋ ዛዴ የተፈለገውን የኮምፕዩተር ተግባር ስምን ለቤተመቅደስ ማዘጋጀትን ጭምር ይሰራላችዋል። ለናንተ ወደ ስልሳሺ የሚጠጉ ናቸው።

አድሱ የቤተሰብ ፍለጋ ዛዴ የቤተሰብ ታሪክ ሥራ ሂዴትን ይለውጣል፤....ባለፉት ሰዎች የራሳቸውን መረጃ ለብቻ ያስቀምጡ ነበር። አንዳንዴም ሌሎች የቤተሰብ አባሎች ሳያውቁ የሰሩ ይሆናል። አሁን እያንዳንዱ ሰው ከሌሎች ጋር በመስራት ለቤተሰብ ዛፍ መረጃ አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ።

ምንም እንኳ የቤተሰብ ፍለጋ አስፈላጊ ቢሆንም ደርጃ አለው። የበለጠ ሥራ አለ። ምክንያቱም ለብዙ አስርተ አመታት ለቤተክርስትያን የተሰጠው መረጃ በአድሱ የቤተሰብ ፍለጋ የተባዛ ሆኖ ስህተት ልያመጣ ይችላል። ለቀድሞ ሰፋሪዎች የሚመጣው

ጠቃሚ ይሆናል። የተባዙ ስህተቶች መስተካከል ይገባቸዋል። ከያንዳንዱ ቤተሰብ የተሻለ የሚሰራ የለም።

በዚህ የፈተና ሥራ ተስፋ ልትቆርጡ ይሆናል። የራሳችሁ ጉዳይ በደንብ እንደተረዳ እርግጠኛነት ይኑራችሁ። ቤተክርስትያኑ በተነበየ አመራራት ፕረዚዳን ቶማስ ኤስ ሞንሰን ሥር ይህን ችግር ለመፍታት በትጋት እየሰሩ ናቸው። በአንድነት የቤተሰብ ዛፍን ለእግዝአብሄር ልጆች ለማደራጀት እንሞክራለን። ይህ ከፍ ያለ ጥረት፣ ከፍ ያለ ወሮታ አለው።

ይህ የሚያስደት ሥራ ነው። ይህን የአድስ አባሎች ፎቶ ለዘራቸው የቤተመቅደስ ሥራ መሥራታቸውን ተመልከቱ። እንኝህ ወድ ቅዱሳን ከኤልሳቫዶር ስቴክ ጓትማላ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተመቅደስ ተካፋይ ሆነዋል። የቤተመቅደስ መታወቂያ በመያዝ የሞቱትን ዘመዶች ስም ወኪላዊ ጥምቀት ፈፅመዋል።

የቤተክርስትያን የቤተሰብ ታሪክ ጥረት እንድሳካ የክህነት ሥልጣን እና አመራራት አስፈላጊ ናቸው። መሪዎች መሰረታዊ የሆነውን የቅዱስ ሥራ በማስተማር ይመስክራሉ። ያለውን መመሪያ በመመልከት ሹመትን ይሰጣሉ። የዎርዳቸውን መንፈስ ለማንሳት ስለ ቤተመቅደስ እና ቤተሰብ ታሪክ እንቅስቃሴ በማስብ ለአድስ አባሎች መንፈሳዊ ብርታትን በመስጠት የሁሉንም አባሎች ህይወት ይባርካሉ።

ቤተመቅደስና የቤተሰብ ታሪክ ሥራ በመንፈስ አለም ያሉትን እንደሚባርክ ኗሪ የሆኑትንም በእኩል ሀይል ይባርካቸዋል። ተሳታፍ የሆኑትን የማንፃት ተሰሚነት አለው። እንሱም ቤተሰባቸውን ለማስደሰት ይረዳሉ።

በሀያሉ እግዛብሄር ፍት ከቤተሰባችን ጋር ስንሆን እንደሰታለን። ነቢይ ጆሴፍ ስሚዝ ሥራችንን አይተዋል። የጌታ ታልቁ ቀን እየመጣ ነው አለ፤ ስለዚህ እንደ ኋለናው ቀን ቅዱሳን ለጌታ በቅዱስነት ስጦታን እንሰጣለን እናም ከማንኛውም በላይ ዋጋ ያለውን የሙታን መረጃ የያዘ መፅሀፍም ለቤተመቅደስ እናቀርብ።

መረጃውን የማዘጋጀት የግለኝነት እና የጋራችን ሀላፍነት ነው። በአንድነት እየሰራን በጌታ ፍት ብቁ ሆነው እንድቀርቡ እናደርጋለን። ይህ መረጃ ሥርዓቶች እንድፈፀሙ በማድረግ የሞቱትም በምርጫቸው ልቀበሉ ይችላሉ። ይህም ሥርዓቶች ለምርኮኞች ነፃነትን ያመጣል

የልጅ ልጆቻችን ወድ ሩብ እና ሁሉም የልጅ ልጆቻችን በፍቅር ተያይዘዋል። ከቅድመ አያቶቻቸውም በፍቅር ተያይዘዋል። ይህ መያያዝ ወደ ዘላለማዊ ቤተሰብነት ወደ ሚመራው በቅዱስ ሥርዓቶች ተበይደዋል። ይህ ቅዱስ አላማ እያንዳንዳችን ይታወቅ ዘንድ ፀሎቴ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን።